# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# ኢየሱስ ታላቁ መምህር




ጸሐፊው: Edward Hughes
የተተረጎመው: Eyerusalem Dechasa
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.



ታሪክ 42 ከ 60 ዎቹ መሃከል

www.M1914.org

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


አማርኛ

Amharic



ኢየሱስ ታላቁ እና ምርጡ መምህር ነው። ብዙ ሰዎች ኢየሱስን አዳምጠውታል። ኢየሱስም መሐሪ, ጥሩ እና ደግ እንዲሆኑ ይነግራቸው ነበር።

1



ሌሎቹ ይጠሏቸው እንዲሁም ይጎዷቸው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይንከባከባቸው ነበር።

2


ኢየሱስ ብዙ ነገሮችን ለህዝቡ ያስተምር ነበር። የእግዚአብሔር ህዝቦች ሻማ ቤትን በሚያበራበትን መንገድ ለአለም ማብራት እንዳለባቸው ያስተምራቸው ነበር። ሻማ በጨለማ ክፍል ውስጥ ያለው ልዩነትንም አስረዳቸው።
3


ኢየሱስም ለህዝቦቹ "ዓይን ስለ ዓይን, ጥርስ ስለ ጥርስ" ብሎ ስለበቀል አስተማራቸው። ሆኖም ግን ኢየሱስ ለጠላቶቹ እንኳ ደግነትን፣ ይቅርታን እና ፍቅርን አስተማረ።
4


በኢየሱስ ዘመን አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን በጣም ቅዱስ እንደሆኑ አድርገው ያቀርቡ ነበር።
5


ለለማኞች ገንዘብ ሲሰጡ አንድ ሰው መለከት እንዲነፋ ያደርጉ ነበር በዚህም ሁሉም ሰው እንዲያያቸው ያደርጉ ነበር።
6


ኢየሱስም "የምትሰጡትን ስጦታ በድብቅ አድርጉ እግዚአብሔርም ይከፍላችኋል" አላቸው።
7


ኢየሱስ ስለ ጸሎት ተመሳሳይ ነገር አስተማረ። አንዳንድ ሰዎች በጎዳናዎች ማቆሚያ ስፍራዎች ይጸልያሉ ስለዚህ ሁሉም ሰው ያያቸዋል፣ ይሰማቸዋል። ስለ እግዚአብሔርም ግድ የላቸውም።
8


ግድ የሚላቸው ሰዎች ስለነርሱ የሚያስቡት ነገር ነበር። ኢየሱስም እነርሱን ሂፖክራይት በማለት ሰየማቸው። ትርጓሜውም ሀሰተኛ ተዋናዮች ማለት ነው።
9


ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ለትምህርቶቹ ተፈጥሮን እንደምሳሌ ተጠቅሟል። ለምሳሌ, ወፎቹን ጠቅሷል። "የሰማዩ አባታችው ይመግባቸዋል" ብሏል። "አትጨነቁ ለእናንተም እንዲሁ እግዚአብሔር ይመግባችኋል።"
10


ኢየሱስ "ባለፀጋው ንጉሥ ሰሎሞን እንኳን እንደ አበቦች የደመቀ ልብስ አልለበሰም" በማለት ቀጠለ። "እግዚአብሔር ሜዳን በሣር ካለበሰ እናንተን እንዴት አያለብሳችሁም?"
11


ኢየሱስ ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የሚያቀርብላቸውን እግዚአብሔርን እንዲታመኑ ያስተምራቸው ነበር።
12


"በወንድምህ የምትፈርድ ከሆነ ይህ ማለት በዓይኖችህ ውስጥ ትልቅ ምሰሶ እያለ የወንድምህን ትንሿን ጉድፍ ለማውጣት መሞከር ማለት ነው። ምናልባት ሰዎች ያሾፉበት ይሆናል። ነገር ግን ትርጉሙን መፈለግ ነበረባቸው።
13


ኢየሱስም ሰዎች የእግዚአብሔርን እርዳታ መጠየቅ እንዳለባቸው ተናገረ። ምድራዊ አባት የተራበ ልጁ ዳቦ ሲጠይቀው ድንጋይ ይሰጠዋል? አይ! መልካም ነገር ይሰጠዋል እንጂ። እግዚአብሔርም እንዲሁ ለሚለምኑት መልካም ነገሮችን ይሰጣቸዋል።
14

ታላቁ አስተማሪ ኢየሱስ ስለ ሐሰተኛ
አስተማሪዎች አስጠነቀቀ። ኢየሱስ
"የበግ ለምድ ይለብሳሉ ውስጣቸው
ግን ተኩላዎች ናቸው" በማለት
ተናገረ። ሐሰተኛ መምህራን በሚኖሩት
ህይወት እንደሚታወቁም ተናገረ።



15

በታሪኩ ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል የሚታዘዙ
ሰዎች ቤቱን በዓለት ላይ የሠራን ሰው እንደሚመስሉ አሳያቸው።
ኃይለኛ አውሎ ነፋስ ተነሳ ነገር
ግን ቤቱ ጸንቶ ቀመ።



16

ሰነፍ ሰው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ ሠራ። ዐውሎ ነፋሱም
መጣ ደካማ መሠረት በመሆኑ ምክንያት ፈራረሰ። ኢየሱስም
የእግዚአብሔርን ቃል የማይታዘዙ እንደዚህ ሰው ናቸው ብሎ
ተናገረ።



17

ሕዝቡም ኢየሱስ በተናገረው ነገር
እጅግ ተደነቁ። ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ
ነገር ሰምተው አያውቁም ነበር። አሁን
የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ ይህ ብቻ
በቂ እንዳልሆነ አወቁ። በየቀኑ መታዘዝ
ይኖርባቸዋል።



18

ኢየሱስ ታላቁ መምህር

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማቴዎስ 5-7፤ ሉቃስ 6

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሳልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16